# የርብራብ ቀፎ አሠራር

## የንቦች ለልማት ኢትዮጵያ ልምድ




### ሥልጠና መስጠት 1

ስለ ርብራብ ቀፎ አንጻራዊ ጥቅሞችና አሠራር በቂ የክህሎት ሥልጠና መስጠት።



### እንጨትና ቁሳቁሶችን ማቅረብ 2

ለርብራብ ቀፎ መስሪያ የሚሆን ሽምበቆ፣ ቅርቅሃ፣ ማገር፣ የመሳሰሉትን እንጨቶችንና ለሥራው የሚያስፈለጉ መጋዝ፣ መጥረቢያ፣ ሜትር፣ ቢላዋ፣ የቃጫ ገመድ (ሲባጎ)፣ ሚስማር ማቅረብ።




### የቀፎውን ርዝመትና ስፋት መወሰን 3

ሠልጣኞችን በቡድን በመከፋፈል እንጨቶችን በልኬታቸው መሠረት አራት ባለ100 ሳ.ሜ፣ ሁለት ባለ 50 ሳ.ሜና ሁለት ባለ 30 ሳ.ሜ ልኬታ መቁረጥ።



### የቀፎውን ጎኖች መሥራት 4

አምስት ባለ 30 ሳ.ሜ ርዝመት እንጨቶች መቁረጥና በሁለቱ ባለ 100 ሳ.ሜ ርዝመት እንጨቶች ላይ ውስጥ ለውስጥ በሚስማር በመምታት በዚህ ዓይነት ሁለት ጎኖችን መሥራትና በቀፎ ርዝመትና ጎን ልክ ሽምበቆ ወይም ቅርቅሃውን በመቆራረጥና በመሰንጠቀ ቀፎውን መገድገድ።



### ቀፎውን መገጣጠም 5

የቀፎውን ሁለት ጎኖች፣ የፊት እና የኋላ ክፍሎችን በሚስማር በማያያዝና በመገጣጠም ቀፎውን መገጣጠም።



### የቀፎውን ስራ ማጠናቀቅ 6

እያንዳንዱ ሰልጣኝ በቡድን እንዲሠራ በተሰጠው ክህሎት መሰረት ቀፎውን ሰርቶ ማጠናቀቅ።



### ቀፎውን መውሰድ 7

በፕሮጀክቱ ድጋፍ በሠልጣኞች የተሰሩ ቀፎዎች ሲወስዱ



### ርብራብ መሥራት 8

እንደቀፎው ርዝመት የ3.2 ሳ.ሜ ስፋትና 50 ሳ.ሜ ርዝመት ያላቸው 30 የሚሆኑ ርብራቦችን ከጣውላ፣ ከማገር፣ ከቀርቅሃ መሥራት።



### የቀፎ ክዳን መሥራት 9

የቀፎዉን ክዳን ሁለት ባለ 105 ሳ.ሜና ሁለት 54 ሳ.ሜ ርዝመት ያላቸው እንጨቶችን በአራት ማዕዝን በሚስማር መገጣጠም፣ ከውስጥ ያለዉን አግዳሚ በእንጨት በመማገር በተሰነጠቁ ሽምበቆዎች መማገር፣ ከላይ በኩል በልሙጥ ቆርቆሮ በሚስማር መምታት።



### ንቦችን ማዛወር 10

በባህላዊ ቀፎ ውስጥ ያሉ ጠንካራ ንቦችን ከላይ በተገለጸው መልኩ በተሠራው ቀፎ ውስጥ ማዛወር፣ በተዘጋጀለት ቦታ ማስቀመጥና ክትትል ማድረግ።







ይህ የርብራብ ቀፎ አሠራርን የሚሳይ ፖስተር የተዘጋጀው በንብ ሃብት ልማት ዘርፍ የመረጃና የምክር አገልግሎት በሚሰጠውና የበጀት ድጋፍ በሚያደርገዉ ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ በሚባል ድርጅት ነዉ። የሽግግር ቀፎ ከአካባቢው ቁሳቁስ በአርሶ አደሩ በቀላሉ የሚሰራ፣ የተሻለ ጥራትና ብዛት ያለው የማርና ሰም ምርት የሚሰጥ የቀፎ ዓይነት በመሆኑ በሰፊው አገልግሎት ላይ እየዋለ ነው። በመሆኑም ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ በርብራብ ቀፎ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በማስፋፋት ላይ ይገኛል።

ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ
ፖ.ሣ.ቁ.786
ሞባይል: 0918761182
ኢ-ሜይል: tilahun_gebey@yahoo.com
ምዕራብ ጎጃም ዞን
ባህር ዳር